የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

# ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ በካይ ጋዝ ቁጥጥር መመሪያ

# ማብራሪያ

መጋቢት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ግቦች ላይ የአለም አማካይ የሙቀት መጠን ለኢንዱስትሪዎች ከ2°C በላይ እንዳይጨምር እና እንደ አጠቃላይ የሙቀት መጠኑ ከ1.5°C እንዳይበልጥ ጥረቶችን ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም በመያዝ አኤአ በ2011 ዓ·ም የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ መስመርን ዘርግታ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ራዕይ ሰንቃ በመንቀሳቀስ ሂደት ላይ ትገኛለች፡፡ በዚሁ ሂደት ሀገሪቱ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ዕድገትን አስመዝግባለች፡፡ ይህ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስትራቴጂ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ላይ እንደ አንድ ስትራቴጂክ ምሰሶ (Stratejic Pillar) ሆኖ ተካቷል:: በተጨማሪም ሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ መፍተሔ የምታበረክተውን አስተዋፅዖ ወይም ሀገራዊ ድርሻ (National Determining Contribution) በማዘጋጀት እና በመከለስ በ 2030 ዓ.ም የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠንን እስከ 68.8% ድረስ ለመቀነስ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እርምጃዎችን እየወሰደች ትገኛለች፡፡

በመሆኑም የሀገራችን የልማት ሥራዎች ከአካባቢና ማኅበረሰብ ልማት ደኅንነት ጋር በተስማማ መልኩ በዘላቂነት ለማስቀጠል መንግሥት በነደፈው ፖሊሲ መሠረት ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልትን አዘጋጅቶ በማስፈፀም ሂደት ላይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥራን ወደ በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ውስጥ አካቶ እየተገበረ ይገኛል፡፡

ይሁንና ከትራንስፖርት ዘርፉ በተለይም ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና የአየር ብክለትን በመፍጠር የተለያዩ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እያስከተለ በመሆኑ የተለያዩ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአየር ብክለትን ለመቆጣጠርና አግባብነት ያለው እርምጃ ለመውሰድ የተሽከርካሪ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጸደቀ ሲሆን ስታንዳርዱን ተግባራዊ ለማድረግ ማስፈፀሚያ የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል ፡፡

## 1. <u>ለመመሪያው መዘጋጀት አነሳሽ ምክንያቶች</u>

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 44 (1) ሁሉም ሰዎች ንጹሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም የአካባቢ ደኅንነት ዓላማዎች አንቀጽ 92 መንግሥት ሁሉም ኢትዮጲያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት እንዳለበት የተደነገገ በመሆኑ፤ ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ የአካባቢውን ደኅንነት የማያናጋ መሆን እንዳለበት፤ የሕዝብን የአካባቢ ደኅንነትን የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልፅ የማድረግ ኃላፊነት፤ እንዲሁም መንግሥትና ዜጎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ እንዳለባቸው የሚደነግግ ስለሆነ፤

ከላይ የተመለከቱትን የሕገ-ምንግሥቱን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በ1995 የወጣው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አካባቢን ሊጎዱ የሚችሉ የልማት እንቅስቃሴዎችን ከተቻለ ማስወገድ ካልተቻለ ደግሞ ተገቢ የሆኑ ተግባራትን በማከናወን ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት መቀነስ አስፈላጊ መሆኑን በመደንገጉ፤

በአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ተ) እና በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) እና አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (28) የትራንስፖርት ዘርፍ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና በአየር ንብረት ላይ የሚኖራቸውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት በሥራ ላይ የማዋል አተገባበራቸውንም የመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠው ለሚኒስቴር መ/ቤታችን ስለሆነ፤

በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዝ ክምችት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት በሚከሰተው የአየር ብክለት ሳቢያ የሰው ልጆች ለተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ችግሮች እየተጋለጡ ስለሆነ፣ ይህንኑ የአየር ብክለትን የሚያስከትለውን ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ችግሮች ለመፍታት ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የትራንስፖርት ዘርፍ አንዱ ሲሆን

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቀውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስና ለመቆጣጠር የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ኃላፊነቱን መወጣት ያለበት በመሆኑ፤

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ከትራንስፖርት ዘርፉ ከተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ በሚለቀቀው የበካይ ጋዝ ልቀት ምክንያት የሚከሰተውን የአየር ብክለት በመከላከል የዜጎችን ጤንነት እና የአካባቢ ደኅንነትን መጠበቅ የሚያስችል ቁራጥ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል ከተሽከርካሪ የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን የሚወስን ሀገር-አቀፍ ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 193/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት እ.ኤ.አ. በ28/12/2022 ስታንዳርዱን ያጸደቀ ስለሆነና ስታንዳርዱን ለማስፈፀም የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12 (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**በአጠቃላይ መመሪያውን ለማውጣት አነሳሽ የሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-**

1) በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀው የሙቀት አማቂ በካይ ጋዝ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ከልማት እንቅስቃሴዎቹ መካከል ዋነኛው ደግሞ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ መሆኑ፤
2) ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን በመጨመሩ ምክንያት ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ የሚገኘው የአካባቢ እና አየር ብክለት፤
3) የአየር ብክለት በሰው ልጆች ላይ የሚያስከትላቸው በኢኮኖሚያዊ እና በማኅበራዊ መስተጋብር ላይ የሚፈጥረው ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ መኖር፤
4) የነዳጅ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር ዋና ዋናዎቹ ናቸው

## 2. <u>የመመሪያው መውጣት አስፈላጊነት</u>

የተለያዩ ጥናቶች እንዲሚያሳዩት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ወደ ከባቢ አየር ከሚለቁ የልማት እንቅስቃሴዎች መካከል አንዱ የትራንስፖርት ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ጥቅም ላይ የሚውለው የነዳጅ ጥራት ዝቅተኛ መሆንና ለብዙ ዓመታት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ያሉ በመሆናቸው ምክንያት ከዘርፉ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀው የበካይ ጋዝ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ ይህም

በመሆኑ የአየር ብክለትን በማባባስ የሰው ልጆች ጤና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እያሳደረ ይገኛል፡፡ ለአብነት ያህልም በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ምክንያት በሀገራችን በተከሰተው የአየር ብክለት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አስተዋጽኦ 10% መድረሱን በምሁራን የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ እነዚህን እና መሰል ችግሮችን መፍታት የሚቻለው የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን በመቀነስ የአካባቢ እና አየር ደኅንነትን በመጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችል የተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ስታንዳርድ የተዘጋጀ ሲሆን ስታንዳርዱን ተግባራዊ ለማድረግ፤ ለማስፈፀም እና ለመፈፀም መመሪያውን ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 3. <u>መመሪያውን በማውጣት ማሳካት የተፈለገው አላማ</u>

የተሽከርካሪዎች በካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ የአፈፃፀም መመሪያ በማውጣት ማሳካት የተፈለገው ዋና ዓላማ ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን በመቀነስ እና የአካባቢ ደኅንነት እና የአየር ብክለትን በመከላከል የዜጎችን ጤንነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንንም በዝርዝር ስናይ፡-

1) ከተሽከርካሪ የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን በመቀነስ የኅዝብ ጤንነት ማስጠበቅ፤
2) ከተሽከርካሪ የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን በመቀነስ የአካባቢ ደኅንነትን እና የአየር ብክለትን መከላከል እና መቀነስ፤ እና
3) የበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙት የነዳጅ ፍጆታን መቆጠብ እና የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ወጪ መቀነስ፤ የሚሉትን ዓላማዎች በውስጡ የያዘ ነው፡፡

## 4. <u>ረቂቅ መመሪያውን ለማዘጋጀት የተገኙ ግብዓቶች</u>

1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 44 እና 92
2) በ1995 የወጣው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ አዋጅ ቁጥር 300/1995
3) በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጸደቀው የተሽከርካሪዎች በካይ ጋዝ ልቀት መጠን ስታንዳርድ (በ28/12/2022 እ.ኤ.አ.)
4) የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣
5) የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014፣

## 5. ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብዓቶች

### ሠንጠረዥ1፡-ተቀባይነት ያገኙ እና ያላገኙ አስተያየቶች ከነምክንያቶቻቸው፡፡

| ተ.ቁ | ከባለድርሻ አካላት የተነሱ ነጥቦች /አስተያየቶች/ | ተቀባይነት ያገኙ ሐሳቦች ከነምክንያታቸው | ተቀባይነት ያላገኙ ሐሳቦች ከነምክንያታቸው |
|---|---|---|---|
| 1 | ከተሽከርካሪዎች እየተለቀቀ ያለው የጭስ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ አንዳንዶቹ ተሽከርካሪዎች ስታንዳርዱም ሳያስፈልግ በአይን ብቻ በማየት መለየት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ስላለን ስታንዳርድ መዘጋጀቱም ሆነ የማስፈፀሚያ መመሪያ መቅረቡ ትክክል እና አስፈላጊ ነው፡፡ | አስተያየቱ መመሪያውን የሚደግፍ እና የሚያበረታታ ስለሆነ ተቀባይነት አግኝቷል | |
| 2 | ማስፈፀሚያ መመሪያ ላይ ከተቀመጡት ዓላማዎች በተጨማሪ ለማኀበረሰቡ ጤና መጠበቅ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ቢካተት | የመመሪያው አንዱና ዋናው ዓላማ የኅብረተሰቡን ጤና መጠበቅ በመሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል | |
| 4 | ስታንዳርድን በየጊዜው ማሻሻል ይቻላል፤ መመሪያ ድግሞ ብዙ ጊዜ አይሻሻልም፤ ስለዚህ መመሪያው ላይ የኢትዮጵያን ስታንዳርድ ያሟላ እየተባለ ቢጠቀስ | | በመመሪያው ላይ ስታንዳርዱን እየተባለ ቢጠቀስም ትርጓሜ ላይ ስታንዳርድ ማለት በኢትዮጵያ የጸደቀው ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን መወሰኛ መሆኑን ስለሚያብራራ ተቀባይነት አላገኘም |
| 5 | መመሪያው ላይ በገንዘብ ይቀጣል የሚለው ቢብራራ ለምሳሌ ስንት እንዴት በሚል ቢገለፅ | የድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ የቅጣት አፈፃፀም ተግባራዊ ይደረግበታል የሚል እንጂ በገንዘብ ይቀጣል የሚል መመሪያው ላይ ያልተቀመጠ መሆኑ ተብራርቷል | |
| 6 | እንደ ሀገር የተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት መነሻ (ነባራዊ ዳሰሳ) ስለመሰራቱ ማብራሪያ ቢሰጠን | ነባራዊ ዳሰሳ ስለመሰራት የሚያብራራ ክፍል ባለመኖሩ የተነሳ ጥያቄ ሲሆን ማብራሪያ ተሰጥቷል | |
| 7 | ወደ ሀገሪቱ የሚገባው የነዳጅ ጥራት እየታወቀ “ጥራት ያለው ነዳጅ መጠቀም” የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ግዴታ ሊሆን አይገባውም | ጥራት ያለው ነዳጅ ሲባል ቀጥተኛ ፍቺውን በመውሰድ የተጠየቀ ጥያቄ ሲሆን ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ ጥራት ያለው ነዳጅ ሀገሪቱ ከምታስገባው ከሕጋዊ ቦታ በመግዛት መጠቀም አለበት በሚል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ተስተካክሏል | |
| 8 | የቦሎም ሆነ የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራ በተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ቢከናወን የህብረተሰቡን የገንዘብ እና የጉልበት ወጪዎችን ያስቀራል | የቦሎም ሆነ የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራ በተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ማከናወን የሚቻል መሆኑን ነገር ግን ውድድር በመፍጠር ጥራት ያለው ምርመራ ተቋማት እንዲፈጠሩ የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራን ብቻ የሚሰሩ ተቋማት ቢቋቋሙ አስፈላጊ መሆኑ ተብራርቷል | |
| 9 | ለበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን ጥራት የሚያረጋግጠው አካል ማነው? | የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት መሆኑን ምላሽ ተሰጥቷል | |
| 10 | መመሪያው የተሽከርካሪዎችን እድሜ ያመከለ መሆን አለበት | | የተሽከርካሪዎች እድሜም ሆነ የመጫን አቅም ስታንዳርዱ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም |
| 11 | የቅሬታ አቀራረብ ላይ በ7 ተከታታይ ቀናት ምላሽ ይሰጣል የሚለው የቅሬታ አቅራቢውን መብት አያረጋግጥም (የፈጻሚውን አካል ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዳይሆን ቅሬታ ለማቅረብ ክፍት መሆን አለበት) | | |
| 12 | ለበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን የሚያቀርበውና የሚገጥመው አካል አንድ ነው ወይስ የተለያዩ ናቸው | የቴክኖሎጂ መሳሪያ አቅራቢና ገጣጣሚ ድርጅት አንድ ሊሆንም ላይሆንም እንደሚችል ተብራርቷል | |
| 13 | መስፈርቶች ላይ በተሽከርካሪው መሟላት ያለባቸው በሚል የተለያዩ መስፈርቶች ተቀምጠዋል መስፈርቱ ሳይሆን ቁጥሩ ቢቀመጥ- | | ቁጥሩ ስታንዳርዱ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም |
| 14 | ሀገር አቋራጭ ተሽከርካሪዎች ላይ ፍቃድ የተሰጣቸው በፌደራል ሆኖ እያለ በጉዞ ላይ እያሉ በድንገተኛ ፍተሻ የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃን ባያሟሉ በክልል/ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ሊጠየቁ አይገባም | የክልልም ሆነ የከተማ አስተዳደር የድንገተኛ የበካይ ጋዝ ልቀት ፍተሻ ማድረግና እርምጃ መውሰድ የሚችለው ፍቃድ ለሰጠው ተሽከርካሪ ብቻ መሆኑን ማስተካከያ ተደርጓል | |
| 15 | የእርምጃ አወሳሰድ ሂደቶችን በሚመለከት ተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃን ሳያሟሉ ቢቀሩ እንዲያስተካክል 7 የስራ ቀናት ይልና ሌላ ቦታ ላይ 10 የስራ ቀናት እንዲሁም 4 ወር የሚል አለ ግልፅ ቢሆን- | ሦስቱም የጊዜ ገደቦች የተቀመጡት በተለያየ ቦታ ለተለያየ ዓላማ በመሆኑን በማብራራት ጥያቄው መልስ አግኝቷል | |
| 16 | መመሪያው ላይ ተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃን ሳያሟሉ ቢቀሩ የፊትና የኋላ ሰሌዳ ተፈቶ | የተነሳው ጥያቄ ትክክል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 10 የስራ ቀናት ይገደባል ይላል፤ ሁለቱንም ሰሌዳ መፍታቱ ከህግና ደንብ አንፃር ቢታይ- | በመሆኑና የፊትና የኋላ ሰሌዳ መፍታት ከህግ አንፃር አግባብነት ስለሌለው የፊት ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ መመሪያው ላይ ተስተካክሏል | |
| 17 | ስታንዳርዱን ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ከወጣ ማስፈፀሚያ መመሪያውንም ቢያዘጋጅ | | ስታንዳርዱን ማውጣት የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ተግባርና ሀላፊነት ሲሆን ማስፈፀሚያ መመሪያውን ማዘጋጀት ደግሞ የስራው ባለቤት የትራንስፖርት ተግባርና ሃለፊነት በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም |
| 19 | እኛ ዋና ባለድርሻ አካል እንደመሆናችን ምን ዓይነት ድጋፍ ታደርጉልናላችሁ | ስልጠናዎችን የመስጠት፤ መረጃ የመስጠት እና ሌሎችንም ድጋፎች በማድረግ ድጋፍ የሚደረግ መሆኑ ተገልጿል | |
| 20 | ተሽከርካሪዎች በምርመራ ወቅት የበካይ ጋዝ ልቀት ስታንዳርድን አሟልተው በድንገተኛ ፍተሻ ወቅት ስታንዳርዱን ባያሟሉ የምርመራ ተቋማት ለምን ይጠየቃሉ | | የተነሳው ጥያቄ መመሪያው ላይ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም |
| 21 | የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራው በዓመት ሁለት ጊዜ ቢሆን | | በተጨማሪም የቦሎ ምርመራ የሚካሄደው በዓመት አንድ ጊዜ በመሆኑ እና ከኢኮኖሚም ሆነ ከተግባራዊነት አንፃር ስለሚያስቸግር ተቀባይነት አላገኘም |
| 22 | የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራ የደቂቃ ስራ ሆኖ እያለ ስታንዳርዱን ሳያሟላ የቀረ ተሽከርካሪ ከእንቅስቃሴ የሚታገድበት ቀን በዝቷል | የመጨረሻውን የቀን ገደብ የተቀመጠ መሆኑን እና ተሽከርካሪው ብቁ ሆኖ እስከተገኘ ደረስ በማንኛውም ሰዓት እገዳው የሚነሳለት መሆኑ ተብራርቷል | |
| 23 | ምርመራ ተቋማቱ የሚጠየቁበት አግባበብ ላይ ሰፋ ብሎ ቢታይ ለምሳሌ አንድ ባለሙያ ቢያጠፋ አጠቃላይ ተቋሙ መዘጋት የለበትም | ምርመራ ተቋማት ላይ እርምጃ የሚወሰደው በአንድ ጊዜ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ መሆኑ ተብራርቷል | |
| 24 | የበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ ቴክኖጂዎችን በሚመለከት መጠየቅ ያለበት ተጠቃሚው ሳይሆን አስመጪው መሆን አለበት | | አስመጪው የሚጠየቅ ቢሆንም ተጠቃሚው ፈቃድ ከተሰጠው አካል መግዛት ያለበት በመሆኑ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ተቀባይነት አላገኘም |
| 25 | የአዲስ አበባ የአየር ብክለት ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን የሚያሳዩ መሳሪያዎች አሉ፤ የተለያዩ ጥናቶች ውጤትም የሚያሳየው የተለያዩ በሽታዎች የሚመጡት በአየር ብክለት ምክንያት መሆኑን ነው፤ ስለዚህ መመሪያው መውጣቱ አስፈላጊ ነው። የአየር ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ የሚሉት ልዩነት ስላለቸው ቢስተካከል- | የአየር ንብረት ለውጥ በሚል የተገለፀው የአየር ብክለት በሚል ተስተካክሏል | |

## 6. <u>የመመሪያው ይዘት</u>

መመሪያው አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህ ክፍሎች በአጠቃላይ 24 ዋና አናቅጽን እና በእያንዳንዱ አንቀጽ ስር እንደ አስፈላጊነቱ በርካታ ንዑሳን አናቅጽ ይገኙበታል። በአጠቃላይ የመመሪያው ይዘት ዘርዘር ተደርጎ ሲገለፅ የሚከተሉትን ርዕሰ-ጉዳዮች በማካተት ተዘጋጅቷል። መመሪያው አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፡-በክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን፣ በክፍል ሁለት በተለያዩ አካላት የሚፈፀሙ ተግባራትን፣ በክፍል ሦስት ስለተለያዩ አካላት ግዴታዎችን፣እና በክፍል አራት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ይዟል።

## 7. <u>ማጠቃለያ</u>

በአጠቃላይ በረቂቅ መመሪያው ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቂ ውይይት የተደረገ ሲሆን በውይይት በድረኩም ላይ ለተሰጡት አስተያየቶች እና ለተነሱት ጥያቄዎች በኃላፊዎች ተገቢው ማብራሪያ እና ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ አብዛኞቹ ከባለድርሻ አካላት የተሰጡ አስተያየቶች ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር እንደ ግብዓት ተወስደው መመሪያው ተዘጋጅቷል፡፡